


# የደብረ ሰላም መድኃኔዓለም ቤተክርስቲያን የሥራ አመራር ቦርድ መልዕክት

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ፤ አሜን።

ደብረሰላም መድኃኔዓለም የኢ.ኦ.ተ.ቤ.ክ በከተማችን የመጀመሪያዋ ቤተክርስትያን ሆና ከተመሠረተች ጊዜ አንስቶ በተለያዩ ምክንያቶች በስደት ወደ ሚኒሶታ ግዛት ለመጡ ኢትዮጵያውያን እና ትውልደ ኢትዮጵያውያን እጅግ በርካታ መንፈሳዊና ማኅበራዊ አገልግሎቶችን ስትሰጥ ቆይታለች፤ አሁንም በመስጠት ላይ ናት።

በጥቂት መንፈሰ ቀና ክርስትያኖች እና ሃገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን የተመሠረተችው ይህች ቤተክርስትያናችን ዛሬ በመቶዎች የሚቆጠሩ አባላትን እና ተመሳሳይ ቁጥር ያላቸው ተገልጋዮችን ዘርፈ ብዙ የሆነ መንፈሳዊ አገልግሎቶችን እየመገበች ትገኛለች።

በሰንበት ቅዳሴ አገልግሎት የተጀመረው መንፈሳዊ አገልግሎት ዛሬ ከሰንበት በተጨማሪ አምስት ወርሃዊ በዓላት በዋሉባቸው የአዘቦት ቀናት ሁሉ በቅዱስ መድኃኔዓለም፣ በቅድስት ማርያም፣ በቅድስት ኪዳነ ምሕረት፣ በቅዱስ ሚካኤል እና በቅዱስ ገብርኤል እለታት የቅዳሴ አገልግሎት ከመስጠት ባሻገር አመቱን በሙሉ 365 ቀናት ክፍት ሆና በሚኒሶታ እና አካባቢው ለሚኖሩ የ ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ እምነት ተከታዮች ሁሉ አገልግሎት በመስጠት ላይ ትገኛለች።

ደብራችን ሜኒሶታ ደብረ ሰላም መድኃኔዓለም ቤተክርስቲያን በብዙ መቶዎች የሚቆጠሩ ሕፃናት ክርስትና ተጠምቀውባታል በርካቶች ቅዱስ ጋብቻን ፈጽመውባታል በርካቶችም ወደማያልፈው ዓለም ተሸጋግረውባታል።

ቤተክርስቲያናችችን መሠረቷ ጣራና ግድግዳዋ አምላካችን እና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መሆኑን በማስተማር፤ የቤተክርስቲያንን ቀኖና እና ሥርዐት ጠብቃ እየተጓዘች ያለች እና ከመንፈሳዊ አገልግሎት ሌላ ምንም አይነት ተልእኮ የሌላት በመሆኗ የተገልጋዮቿ ቁጥር ከእለት ወደ እለት በከፍተኛ ደረጃ እያደገ መምጣቱ ይታወቃል።

ይህን ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ የመጣውን የምእመናን ቁጥር በበቂ ሁኔታ ለማስተናገድ፤ በተመሳሳይም እያደገ እና እየተስፋፋ በመሄድ ላይ ያለውን መንፈሳዊ አገልግሎትም በተሟላ መልኩ ማቅረብ፤ በተለይም ደግሞ ትውልደ ኢትዮጲያውያን ሕፃናትን በተገቢው መንገድ ሃይማኖታቸውን እና ኢትዮጵያዊ ማንነታቸውን ለማስተማር ምቹ ሁኔታን ከመፍጠር አንጻር ሰፊና የተሻለ ቤተክርስቲያን መገንባት

አማራጭ የሌለው ሆኖ በመገኘቱ የቤተክርስቲያናችን አስተዳደር ቦርድ የሕንፃ ግንባታ ኮሚቴ በአዲስ መልክ በማቋቋም ኮሚቴው በከፍተኛ ሁኔታ በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛል። እስካሁንም እጅግ አመርቂ ውጤት አስመዝግቧል። በዚህ አጋጣሚም አስተዳደር ቦርዱ ለሕንጻ ኮሚቴው አባላት በሙሉ ያለውን አክብሮት እና ምሥጋና በመላው የቤተክርስቲያናችን አባላት ስም ያቀርባል።

ሁላችንም ዘወትር ልናስብበት የሚገባው ዋናው ጉዳይ ግን ራዕያችን ወደ ተግባር ተለውጦ ማየት የምንችለው በተለይ የቤተክርስቲያናችን አባላት የሆንን ምእመናን እንዲሁም አባልም ያልሆን ሰዎች ነገር ግን የዚህች ታላቅ ደብር ተጠቃሚ ክርስቲያኖች ሁሉ ለዚህ የተቀደሰ ተግባር ቃል የገባነውን አስተዋጽዖ በወቅቱ መፈጸም ስንችል ነው።

ዘርፈ ብዙ መንፈሳዊና ማኅበራዊ አገልግሎት የሚሰጥ ትልቅ ተቋም መገንባት የሚቻለው ከገንዘብ አስተዋጽዖ በተጨማሪ በጊዜ በጉልበትና ተጨማሪ ድጋፎችን በማፈላለግ ከፍተኛ ርብርብ ስናደርግ ስለሆነ ይህን መልዕክት ለሚያነቡ ሁሉ የቤተክርስቲያናችን አስተዳደር ቦርድ ለዚህ የተቀደሰ ሥራ በምትችሉት አቅም ሁሉ በመሳተፍ የበረከቱ ተካፋይ እንድትሆኑ ጥሪ ያቀርባል።

ታላቁ ሰው ነህምያ በቅዱስ መጽሐፍ ውስጥ መጽ.ነህ. ምዕ. 2 ቁ. 20 ላይ፦

"እኛ ባሪያዎቹ ተነስተን እንሰራለን የሰማይ አምላክ ያከናውንልናል" እንዳለ እኛም የእግዚአብሔር ምሥጋና የሚቀርብበትን ቅዱስ ሥጋውና ክቡር ደሙ የሚፈተትበትን በስደት ሐገር የተወለዱ ልጆቻችንም በእምነት እና በምግባር ታንጸው የሚያድጉበትን የእግዚአብሔር ቤተክርስቲያን ሰርተን ለፍጻሜ እንደምናደርስ እናምናለን።

ስብሐት ለእግዚአብሔር ወለወላዲቱ ድንግል ወለመስቀሉ ክቡር፤አሜን።



# እናስተዋውቃችሁ



በዛሬው የማዕዶት ዕትማችን የቤተክርስቲያናችን ግንባታ ከፍተኛ አስተዋጽዖ እያደረጉ ከሚገኙት ግለሰቦች መካከል የላቀ ተሳትፎ እያደረገ የሚገኝ በዕድሜው አንቱ ለመባል ያልደረሰ ነገር ግን በምግባሩና ለሌሎች አርአያ በመሆን በሚያደረገው አስተዋጽዖ አንቱ ሊባል የሚገባው እንዲሁም በግል ሕይወቱ፤ በቤተሰብ ሀላፊነቱ ፤ በቤተከርቲያናችን ግንባታ ላይ በሚያደርገው ተሳትፎ ለብዙዎች ምሳሌ ሊሆን የሚችል የቤተክርስቲያናችን አንጋፋ አባል እና ቤተክርስቲያን ግንባታ ሂደት ጊዜውን ፤ገንዘቡን ፤ ሙያውን እየለገሰ የሚገኘው ወንድማችን ኢንጅነር ብርሀኑ በለጠ ይሆናል ። ኢንጅነር ብርሀኑ መድኃኔዓለም ለህይወቱና ለአገልግሎቱ ጉልበት መሆኑን መድኃኔዓለምን ያለ ከመድኃኔዓለም ጋር አብሮ ፀንቶ መኖር እንደሚገባው አጽንቶ ይናገራል። ለግንባታው የሚደረገው የገንዘብ ማሰባሰብ ጥረት አብሮ መስራትን፤ቤተሰባዊነትን ፤መቻቻልን ፤አብሮ ሙብላትን ለማዳበር በር መክፈቱን በግሉም የቤተክርስቲያናችን ወንድሞች እና እህቶቸ ጋር ለመተዋወቅ ዕድል ማግኘቱ እንዲሁም በጋራ ለአንድ ዓላማ ሰዎች ሲተባበሩ ማየቱ ለሚያከናውነው ሥራ ትልቅ የሞራል እገዛና ፍቅር እንዲያደርበት አስተዋጽዖ ማደረጉን በደሰታ ያወሳዋል። ማዕዶት ከኢንጅነር ብርሃኑ ጋር ያደረገቸውን ቆይታ በመጋበዝ መልካም ንባብ ትመኛለች

**ማዕዶት**: እስኪ ከአንተ እንጀመር ብርሀኑን አስተዋውቀን?

**ኢንጅነር ብርሀኑ** : ውልደቴም እድገቴም በሲዳሞ በምትገኘው በዲላ ከተማ ነው። ያሳደጉኝም ወላጅ አባቴ አቶ ዳዲ በለጠ እና እናቴ ወ/ሮ የሹምነሽ አለማየሁ ናቸው። አዲስ አበባ ዩንቨርስቲ ከመግባቴ በፊት በዲላ ሁለተኛ ደረጃ እና ዲላ አግሮ ቴክኒካል ኢንስቲቱት ተምሬአለሁ። በአዲስ አበባ ዩንቨርስቲ የአንድ አመት ቆይታ በኋላ በኬኒያ አምስት የስደት ዓመታትን በማሳለፍ በ 1995 ወደ እዚህ ሀገር የመምጣት እድል በማግኘቴ ላለፉት 22 ዓመታት በሚኒሶታ ኖሬአለሁ። በትምህርት ዓለም በ1999 በአሶሺዮት ዲግሪ ፣ በ2003 ከዩቨርስቲ ሚኒሶታ በኤሌትሪካል ኢንጅነሪንግ ድግሪ በ2009 ደግሞ በቴለኮም ኢንጅነሪንግ የማስተርስ ድግሪዬን አግኝቻለሁ። በ 2001 ዓ/ም በዚሁ ቤተክርስቲያን ከባለቤቴ ከወ/ሮ ዓይናለም ጋር ትዳር በመፈጸም የአራት ሴቶች ልጆች አባት ለመሆን በቅቻለሁ ። በስራ ዓለም የተለያዩ ቦታዎች የመስራት ዕደሉ የገጠመኝ ሲሆን ከ2012 ጀምሮ በዲፓርትመንት ኦፍ ኮሜርስ የፓተንት ክፍል ውስጥ በመስራት እገኛለሁ።

**ማዕዶት**:ለዛሬው ማንነትህ ከፍተኛ ተጽኖ ያሳደሩብህ ሰዎች እነማን ናቸው?

**ኢንጅነር ብርሀኑ** : ለዛሬ ማንነቴ ብዙ ሰዎች ከጀርባው አሉ ቤተሰቦቼ፤ መምህሮቼና ሌሎችም ሰዎች ። ይሁን እንጂ ትልቁን ድርሻ የምትወስደው ባለቤቴ ነች። ባለቤቴ ወ/ሮ አይናለም ትባላለች ለእኔ ጥሩ አመለካከትና ለምወስነው ውሳኔዎች ድጋፍ እና እገዛ የምታደርግልኝ እንዲሁም ከጎኔ በመሆን የምታብረታታኝ በመሆኑ በጣም አመሰግናታለሁ።

**ማዕዶት**: የደብረ ሰላም መድኃኔዓለምን ደብር የተቀላቀልከው መቼ ነው? ከቤተክርስቲያኗስ ጋር ያለህ ግንኙነት ምን ይመስላል?

**ኢንጅነር ብርሀኑ** : ወደ ቤተክርስቲያኗ የመጣሁት በ1999ዓ/ም ሲሆን በአዛን ወቅት ቤተክርስቲያኗ ሚኒያፖሊስ ከተማ በ14ኛው እና በ26ኛው መንገድ መካከል ነበር የምትገኘው። ካህኑ አቡነ ዳንኤል የነበሩ ሲሆን ፤ አቶ በትረ ፤አቶ ታየ፤ በላይነህ ፡ገሊላ ፡ሶስና ና አቶ ተፈራ በቤተክርስቲያኑ ውስጥ የጎላ ተሳትፎ ያላቸው ነበሩ ። ወቅቱም ልክ እንደ አሁኑ ቤተክርስቲያን ለመግዛት ከፍተኛ ጥረት የሚደረግበት ጊዜ የነበረ በመሆኑ የምዕመናኑ ህብረት የሚያስቀና ነበር። ብዙም ሳንቆይ ቤተክርስቲያን መግዛቱ ሲነገረን አሁን ያለንበትን ቤተክርስትያን በማዘጋጀቱ እና መኪናዬን በማቅረብ ዕቃ በማጓጓዝ ተሳትፎ አድርጌለሁ ። ኮ/ል ቢጋሻው የቦርድ ሊቀመንበር በነበሩበት ዘመን በንብረት ክፍል ወስጥ በሀላፊነት ሰርቻለሁ በአሁኑ ወቅት ደግሞ በህንጻ ግንባታ ኮሚቴ ስር በሚገኘው የሕንጻ ዲዛይን ንዑስ ኮሚቲ እንዲሁም በታርጌት ሴንተር ና በዩኤስ ባንክ ስታድዮም የሚደረገውን የነፃ አገልግሎት በማሰተባበርና በመሳተፍ እገኛለሁ።

**ማዕዶት**: በቤተክርሰቲያኑ ግንባታ ከፍተኛ አገልግሎት እያከናወኑ ካሉት ግለሰቦች መካከል ብርሀኑ ትልቁን ድርሻ የሚወስድ ነው ብለው ሰዎች ይናገራሉ በዚህም ምክንያት የህዝብ ግንኙነት ክፍሉም በእዚህ መጽሄት ላይ እንድትወጣ መርጦሃል በዚህ ምን ይሰማሀል?

**ኢንጀጅነር ብርሀኑ** : እኔ ለመድኃኔዓለም በገባሁት ቃል መሰረት ነው እየሰራሁ ያለሁት ቤተክርስቲያን የሚሰሩት የተመረጡ ሰዎች ናቸው ይባላል ከነዚህ አንዱ እንድሆን ምናልባት እግዚአብሔር መርጦኝ ይሆናል ። ሰዎች እኔን አርአያ አድርገው ካስቀመጡኝ እሰየው ነው ሆኖም ሰዎች እኔን ተመልክተው እኔስ የሚል ጥያቄ ለራሳቸው ቢያነሱ ይህን ቤት የማንሰራበት ምክንያት የለም በመሆኑም ሰዎች እኔ ምን ማድረግ እችላለሁ ጥረቱን እንዴት ላግዝ ብለው እንዲነሳሱ እፈልጋለሁ።

**ማዕዶት**: ባለ ትዳር እና የአራት ልጆች አባት ነህ መደበኛ ስራም አለህ በታርጌት ፊልድ ና በዩኤስ ባንክ በሚደረጉት የነጻ አገልግሎቶች ረጅም ሰዓት በመቆየት በተከታታይ ቀኖች በመግባት ሥራዎችን በጥራት በሃላፊነት እየሰራህ ነው የዕለቱን ስራ ከጨረስክ በኋላ ነገ ወይም በመጪው ሳምንት ተመልሶ ለመምጣት የሚኖረው ፍላጎት እንዴት ነው የሚመነጨው ሚስጥሩስ ምንድ ነው?

**ኢንጅነር ብርሀኑ** :እንደማንኛውም ሰው የቤተሰብ ሃላፊ ነኝ መደበኛ ስራም አለኝ እንዲያውም ከስምንት ሰዓት በላይ ነው የምሰራው ትልቁ ሚስጥር ጥረት ነው። የባለቤቴ ከፍተኛ እርዳታም አለበት: ስራው አድካሚ ነው በግለሰብ ደረጃ ከታየ የሚከፍሉን ገንዘብ ትንሽ ነው ትልቁ ነገር ከስራው በስተጀርባ ቤተሰባዊነት፤ አብሮ መስራት ፤ አብሮ መብላት እና መቻቻልን ማወቅ ነው ። መጀመሪያ በስም እንኳን የማንተዋወቅ ሰዎች ዛሬ በስማቸን እየተጠራራን እንዲህ አድርግ አንዲህ አድርጊ በመባባል በፍቅርና በመግባባት ስንሰራ ማየት ደስታን ይሰጠኛል ድካሙን አሰረስቶም ለነገ ያዘጋጀኛል። አሁን በቤተክርስቲያናችን እርስበርስ በመተዋወቅ መቻቻል፤ አይዞህ መባባልንና አብሮ መስራትን ማዳበር እንዲሁም በያንዳንዳችን ስሜት ውስጥ ቤተክርስቲያኗ የኔ ነች የሚል የባለቤትነት ስሜትን ማጎልበቱ ላይ መስራት የሚገባን ይመስለኛል።

**ማዕዶት:** ከገንዘብ ማሰባሰቡ ውጪ የግንባታ ኮሚቴውን እንቅስቃሴ እንዴት ታየዋለህ?

**ኢንጅነር ብርሀኑ** : በነጻ አገልግሎት ከሚደረገው ተሳትፎ ውጪ የዲዛይን ንዑስ ኮሚቴ አባል በመሆን የቤተክርስቲያናቸንን ግንባታ የወለልና ሌሎች ስራዎች ኦርቶዶክሳዊና ኢትዮጵያዊ ለማድረግ ለዲዛይን ተቋራጩ ድርጅት አማራጭ ሰራዎችን ለማቅረብ ከዶክተር ሰናይት ጋር በመሆን የተለያዩ ዲዛይኖችን እየሰራን ነው። የህንጻው ንድፍ ስራ ለወደፊት ሊጨመሩ የሚችሉ ሰራዎችን ለማካተት በሚያስችል መልኩ የሚቀርብ በመሆኑ የጥምቀት በዓልንና በክረምት ወቅት የሚሰተጓጎለውን የታቦት ማውጣት ሰርዓትን ችግር ለመቅረፍ እንዲሁም ሊካተቱ የሚገባቸው ስራዎች ላይ በማተኮር እየሰራን ነው። የግንባታው እንቅስቃሴ በበኩሌ

የተሳካ ነው ብዬ እምናለሁ። በነጻ እገልግሎቱ በአሁኑ ወቅት አንድ መቶ ሀያ ሺ ብር ለማሰባሰብ ችለናል ምንም እንኳን የሚያሰፈልገውን ገንዘብ አሰባስበን ለግንባታ ባንደርሰም እንቅስቃሴው ተስፋ የሚሰጥ ነው ።

**ማዕዶት፡** ለዚህ ቤተከርስቲያን የምትመኘው እና ራዕይህስ ምን ይመስላል?

**ኢንጅነር ብርሀኑ ፡** ምንም እንኳን የተጀመረው የካቴድራል ግንባታ ጥረት ግቡን እንደሚመታና ካቴድራሉ እንደሚሰራ ምንም ጥርጥር የሌለኝ ቢሆንም ይህ ካቴድራል ተሰርቶ ለአንድነታችን መሰረት ሲሆን ማየት እንዲሁም በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስትያናት መካከል ያለው ልዩነት ጠቦ ፍቅራችን በዝቶ ማየት ።

**ማዕዶት፡** ወጣቶችና የተማሩ ሰዎች በቤተክርስትያኑ ግንባታ ግልጋሎት ላይ እንዲሳተፉ ለማድረግ ምን መደረግ ይገባዋል?

**ኢንጅነር ብርሀኑ፡** የሀይማኖት አባቶችና ምዕመናን ወጣቶች እንዲቀርቡ አርአያ መሆን አለባቸው በእምነት ዙሪያ የሚሰጡን

**ኢንጅነር ብርሀኑ ፡** የቫይኪንግ የወደፊት እድል የሚወሰነው በመጪው እሁድ ከፊላደልፊያ ኢግልስ ጋር ቢሚያደርጉት ጨዋታ ነው እሱን ካሸነፉ ለመድኃኔዓለም ስንጥር በማቀበላቸው መድኃኔዓለም ይረዳቸዋል ብዬ አምናለሁ። እሱ ይርዳቸው።

**ማዕዶት፡** በመጨረሻስ የምታሰተላልፈው መልዕክት ካለህ?

ትምህርቶችንና ትውፍሰቶችን በየእለት ህይወታችን በተግባር በማሳየት ለወጣቶች ምሳሌ ካልሆንን ዕምነታችንና ቤተክርስቲያናችንን የሚያስቀጥል ትውልድ ማፍራት ይቸግራል።

**ማዕዶት፡** የነጻ ግልጋሎት ተሳትፎህ በቤተሰብህ ውስጥ ካለህ አስተዋጽዖ ወደ ኋላ አላስቀረህም?

**ኢንጅነር ብርሀኑ፡** በአንድ ወቅት ለሶስት አመታት ከቤተሰቤ ጋር ያልነበርኩበት ጊዜ ነበር ባለቤቴ በረዶ ጠርጋ ሰራዋን ሰርታ ልጆችን ተንከባክባ ተወጥታዋለች ይህን ያነሳሁት የባለቤቴን ድጋፍ ለማሳያት ሲሆን ዛሬም ካለእርሷ ድጋፍ ይህን ለማከናወን ይከብዳል ይሁን እንጂ በእኔም በኩል የጊዜ አጠቃቀሜን በማስተካከል የአባትነትና ያእባወራነት ሀላፊነቴን ሳላዛንፍ አያከናወንኩ እገኛለሁ።

**ማዕዶት፡** በመጨረሻ የቫይኪንግ የሱፐር ቦል ተስፋ ምን ይሆናል ብለህ ትገምታለህ ቫይኪንግ የመድኃኔዓለም ድጋፍ ይኖረው ይሆን? (ይህ ቃለ መጠይቅ የተደረገው ጨዋታው ከመደረጉ በፊት መሆኑን እንገልፃለን)

**ኢንጅነር ብርሀኑ** የማሰተላልፈው መልዕክት በነጻ አገልግሎት ጊዜያቸውን ጉልበታቸውን እያበረከቱ ላሉት የደብረ ሰላም መድኃኔዓለም አባላት ግልጋሎታችሁ ትብብራችሁ ጉልበት፤ ተስፋና ፍቅር እንዲሁም የተሻለም ሰው እንድሆን ሰለረዳኝ እግዚአብሔር ይስጣችሁ እላለሁ።



# ታታሪ ምእመናን በቫይኪንግ ስቴድዮም

የመድኃኔዓለም ምዕመናን የቤተክርስቲያኑን ግንባታ ለማያያዝ የተለያዩ ሃላፊነቶችን በመውሰድ ይህ ነው የማይባል ትልቅ መስዋትነት በመክፈል ላይ ይገኛሉ። ለግንባታው የሚደረገው ተሳትፎ ገንዘብ በማዋጣት ፤ የተለያዩ ዝግጅቶች ላይ በመሳተፍ እንዲሁም በተለያዩ ኮሚቴዎች ላይ የአይምሮና የጉልበት ተሳትፎ ማድረግን ይጨምራል። ምዕመናን በሰፊው ከሚሳተፉበት የገንዘብ ማሰባሰቢያ መንገዶች አንዷና ባለፉት 11 ወራት በተደረገው እንቅስቃሴ ከ120ሺ ብር በላይ ማሰባሰብ የተቻለበት ዘዴ በታርጌት ፊልድ እና በዩኤስ ባንክ ስቴድዮም የነፃ ግልጋሎት በመስጠት የተገኘው ገቢነው። በዚህ ፕሮግራም ላይ ከቤተክርስቲያኑ ጠቅላላ አባላት ግማሽ የሚሆኑ አባላት አንደተሳተፉ መረጃዎች የሚጠቁሙ ቢሆንም በተለይም ቤተክርስቲያን ለመስራት የተመረጡ ምዕመናን ይህ ነው የማይባል ርብርብ እያደረጉ የሚገኙበት ትልቅ ግልጋሎትና በረከት የሚገኝበት ፕሮጀክት ሆኗል ። ይህን ፕሮግራም የተሳካ ለማድረግ ቤተክርስቲያኑ ተገንብቶ ማየት የሚፈልጉ ምዕመናን ከሥራቸው ፤ ከቤተሰባቸው እንዲሁም ከተለያዩ የሶሻል ግዴታቸው እና ተሳትፏቸው ጊዚያቸውን ወስደው ለመድኃኔዓለም በመሰዋት የሚያደርጉት ተሳትፎ እና ጽናት ለብዙዎች የሚያስደንቅ እና የሚያስተምር ነው ። ከተማችን ሱፐር ቦል ባስተናገደችበት ወቅት 80 የሚሆኑ የቤተክርስቲያናችን ምዕመናን በተለያዩ ቀናት ተገኝተው ስልጠናዎችን በመወሰድ ፤ በዕለቱ በሌሊት በመነሳት ፤ረጅሙን የደህንነት ፍተሻ በማለፍ ፤ ከአስራ ስድስት ሰዓታት በላይ ቆሞ በመስራት ለቤተክርስቲያናችን ከአሰራ አምስት ሺ ብር በላይ ሲያስገኙ በህብረታቸው ፤ በጨዋነታቸው ፤ በስራ ስነስርዐታችው ፤ በፈጣን ፤ በቀልጣፋ መሰተንግዷቸውና ጥራት በተሞላው ግልጋሎታቸው የተደሰተው የፕሮግራሙ ባሌቤት መሰሪያቤት( Delware North dports service) አድናቆቱን እና ምስጋናውን በደብዳቤ ገልፆል።



ባለፈው ዕትማቸን በታርጌት ሴንተር የቤተክርስቲያኑ ምዕመናን እያደረጉ ያሉትን የነጻ ግልጋሎት ለመመልከት ሞክረናል በዛሬው ዕትማችን በዩኤስ ባንክ የመደኃኔዓለም ምዕመናን የዕለት ውሎ  በማዕዶት ዕይታ እንደሚቀጥለው ቀርቧል።

ዕለቱ እሁድ ዲሰምበር 17ቀን ነበር ሰማዩ በጭጋግ የተሞላ ሲሆን ቴርሞሚትሩ 28 ዲግሪ ፋራናይት ነበር የሚያነበው። የዕለቱ ግጥሚያ የሚደረገው ከሲነሲናቲው ቤንግልስ ጋር ከቀኑ 12፡00 ሲሆን  ተጫዎቾቹ ከጠዋቱ ሰባት ሰዕት ላይ ምናልባት ከአልጋቸውም ቀና አላሉ ይሆናል በዚህ ጊዜ የነጻ ግልጋሎት የሚያበረክቱ ምዕመናን የሰራ ምድባቸውን መያዝ ያለባቸው ሰዓት ነበር ። ቦታው ለመገኘት በጠዋት ተነስቶ ፤ ፓርኪንግ ፈልጎ ፤ የተወሰነ መንገድ በእግር ተጉዞ የእለቱን ብርድ ለመቋቋም ተዘጋጅቶ መገኘት ይሻ ነበር ። በዕለቱ ለስራ ምድቡ የተሰለፉት ወጣቶች፤ ጎልማሶች፤ እናቶች የዕለቱን የስራ ልብስ ጠቆር ያለ ሹራብ ሱሪና  ጠቆር ያለ ጫማ ለብሰው ሲታዩ ለግልጋሎት ካላቸው ሞራል ጋር ተደምሮ ግርማ ሞገሳቸው የሚያስደስት ነበር፡;

 የቡደኑ ሃላፊና እረዳቶቹ የዕለቱን ስራ የጀመሩት የሚገለገሉባቸውን የተለያዩ ዕቃዎች እና የዕለቱን የምግብ ግባቶች ቆጥሮ በመረከብ ሲሆን ምዕመናኑን ትብብር በተሞላበትና መከባበር በሰፈነበት መልኩ ይህን ካከናወኑ በኋላ በገንዘብ ተቀባይነት በኪችን እንዲሁም በማቀራረብ ምድቦች ተከፋፍለው ጨዋታውን ሊመለከት የሚገባውን ሰው መጠበቅ እንደጀመሩ ተመልካቹ በብዛት በመጉረፍ  የሚጠጣና የሚበላ ለማግኘት ሰልፍ መያዝ ጀመረ።  ከእዛች ሰዓት ጀምሮ ጨዋታው እስከ ሚያልቅ ድረስ ሰልፍ በመያዝ በጨዋታው ልባቸው ተሰቅሎ የፍጥነት ግልጋሎትን የሚሹ ደንበኞችን ተመሰጦ በማዳመጥ እና ስራዐት በተሞላው መንገድ በጥሞና በማስተናገድ ተጠምደው ግልጋሎታቸውን ተወጥተዋል።

ወቅቱ የገና ጾም የነበረ በመሆኑ እና ብዙዎቹም የነጻ እግልገሎት ተሳታፊዎች ጿሚዎች ሰለነበሩ ከድካሙ ተጨማሪ ጾም በዋለ አንጀት የነጻ ግልጋሎት መስጠት ምን ያህል የመንፈስ ጥንካሬ እንደሆነ ሲገናዘብ ይህ ሁሉ መስዋትነት በርግጥም ቤተከርስትያን ለመሰራቱ ማረጋገጫ መሆኑን ማዕዶት ልታሰምርበት ትሻለች።  ጨዋታው በቫይኪንግ አሸናፊነት ከተደመደም በኋላ ተመልካቹ እንደየስሜቱ በመደሰት ወይም በመከፋት ስቴድዮሙን ለቆ ወጥቶ ጸጥታ በሰፈነበት ወቅት ተሳታፊዎቹ መሳሪያዎቻቸውን፤ የስራ ቦታቸውን ሲያጸዳዱ ፤ የተረከቡትን ከሸጡት በማቀናነስ ዕቃዎችንና የምግብ ግባቶችን ሲቆጥሩ የዕለቱን ሽያጭ ሂሳብ ሲያወራርዱ ቆይተው እረጅሙን ሰዓት በትግስትና በትጋት ጨርሰው <<የማያሳፍርም ሠራተኛ ሆነህ የተፈተነውን ሥራህን ለእግዚአብሔር ልታቀርብ ትጋ>> የሚለውን ቃል ፈጸመው ሲሄዱ ውስጣዊ ስሜታቸው ደስተኛ እንደነበር ድካምን ተቋቁሞ ከሚመነጨው ስሜታቸው ይነበብ ነበር።



# የደብረ ሰላም ቤተክርስቲያን ከየት ወደ የት...........

ባለፈው እትማችን የመድኃኒዓለም ቤተክርስቲያን የመመሰረት ሀሳብ እንዴት እንደመነጨ እና በአካባቢያችን የመጀመሪያውን የፀሎት ቤት ለመመስረት የተደረገውን ጥረት እንዲሁም በሚኒያፖሊስና በሴንት ፖል አካባቢ በቀደምትነት የሰፈሩ ኢትዮጵያውያን ሀይማኖታቸውን ለመጠበቅና መንፈሳዊ ግዴታቸውን ለመወጣት ያደረጉትን ጥረትና የቤተክርስቲያን በአካባቢው አለመኖር ያስከተለውን የመንፈስ ችግር ለመዳሰስ ሞክረን ነበር ። በዛሬው ተከታይ እትማቸን ሚኒያፖሊስ በሚገኘው በግሪክ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ውስጥ የፀሎት አገልግሎት እንዴት እንደተጀመረ በሚለው ላይ በማተኮር ከነባር መስራች አባላት ከሆኑት ከወ/ሮ እንዬ ፋንታ ጋር ማዕዶት ያደረገችውን ቃለ ምልልስ በመመርኮዝ የተጠናቀረ ይሆናል። በዚህ አጋጣሚም ማዕዶት ወ/ሮ እንዬ ላደረጉልን ትብብር ከልብ ታመሰግናለች።

በ1987 እዚህ ሀገር በመጣሁ ጊዜ በአካባቢያችን ምንም አይነት ኢትዮጵያዊ የሆነ ቤተክርሰቲያን አልነበረም በዛን ግዜ እኔም መንፈሳዊ ግዴታዬን የምወጣው ወደ ካቶሊክ ቤተክርሰቲያን በመሄድ ነበር በዛን ወቅት ብዙዎቻችን በሲደር አካባቢ እንኖር ሰለነበር የመተዋወቅ እድላቸን ከፍ ያለ በመሆኑ በወቅቱ የምንቀርባቸው የነበሩ እማማ ፈቴ እማማ ሳራ የሚባሉ ለሀይማኖታቸው ቀናዊ የሆኑ ኤርትራዊያኖች የግሪክ ኦርቶዶክስ ቤተክርስትያን አለ ስላሉን በቤተክርሲያኑ ተገኘን። ሰበካው በእንግሊዘኛ ቢሆንም ቅዳሴው በራሳቸው ቋንቋ በመሆኑ በቋንቋ ችግር እንደፈለግነው መከታተል ባያስችለንም አዘውትረን መገኘት ጀመርን ቁጥራችን ሲበረክት የግሪኩ ቤተክርሰቲያን ቄስ ፋዘር ጆርጅ አንድ የራሳችሁ ሰው ቢኖራችሁ በቋንቋችሁ የምትማሩበት ቦታ እናመቻችላችኋለን ብሎ ሃሳብ ሲሰጡን የራሳችን የጸሎት ቤት የመመስረት ሀሳቡ ይበልጥ ተጠናከረ።

በዛው ሰሞን አባ ይስሀቅ የሚባሉ መነኩሴ ለሰርግ ሚኒሶታ መጥተው ነበር በዚህን ጊዜ በጊዜው የነበሩ የኦርቶዶክስ ዕምነት ተከታዮች በከተማው የመጀመሪያውና የራሳቸው የሆነውን የእምነት ቤት እንዲኖራቸው ትልቅ ፍላጎት ስለነበራቸው አባ ይስሀቅን እዚህ ከተማ ቀርተው ቤተክርስቲያን ለመመሰረት እንዲያግዟቸው አጥብቀው ሰለለመኗቸው አባ ይስሀቅም ሰምምነታቸውን በመግለጻቸው የመጀመሪያ የሆነው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቅዳሴና የጸሎት ቤት የሚከናወንበት መርሀ ግብር የግሪክ ቤተክርስትያን እንድንገለገልበት በፈቀድልን ክሃያ እሰከ ሰላሳ ሰው በምትይዝ የህጻናት የመፅሃፍ ቅዱስ ትምህርት መስጫ ክፍል ውስጥ አባ ይስሀቅን በመያዝ ሲጀመር በወቅቱ የቤተክርስትያን ዕውቀት የነበራቸው እቶ በትረም ግሊጋሎቱን በማገዝ ይሳተፉ ነበር ።

አባ ይስሃቅ የመጀመሪያ ቋንቋቸው ትግርኛ ሲሆን በዛች ጸሎት ቤት ይታደሙ የነበሩት ምዕመናን ደግሞ በአብዛኛው የትግራይና የኤርትራ ተወላጆች እንዲሁም የተወሰኑ አማርኛ ቋንቋ ብቻ የሚናገሩ ምዕመናን በመሆናቸው አባ ይስሃቅ በግዕዝ ቅዳሴውን በማሰማት ትምህርቱን በትግርኛ በመቀጠልም በአማርኛ በማድረግ ሁሉንም ሰው ለማስደሰት ሲሞክሩ ጊዜው ሰለሚራዘም በአማርኛ ሲጀመር በትግርኛ የሰሙት ጥለው ሲሄዱ ሌላ ጊዜ ደግሞ አማርኛን በማሰቀደም ትግርኛን ሲያሰከትሉ በአማርኛ ያዳመጡት ትተው መሄድ ሲበዛ አማርኛንና ትግርኛን በማደበላለቅ በማሰተማር የሁሉንም ምዕመናን ስሜት ለመጠበቅ ከፍተኛ ጥረት አድርገዋል።

በግሪክ ቤተክርስቲያን የተጀመረው የጸሎት መርሃ ግብር እንደቀጠለ በአቶ ግርማ ብሩ አማካኝነት አባ ፍቅረማሪያም የጸሎት መርሃ ግብሩን በመቀላቀላቸው ከአባ ይስሃቅ ጋር በመሆን አገልግሎት ሲሰጡና ሲያስተምሩ አማርኛ አንችልም የሚሉ እናቶችን ቅዳሴው በግዕዝ ከተቀደሰ ትምህርት አንድ ጊዜ ነው በማለት እያግባቡ ህዝቡን በደንብ መያዝ ጀመሩ። አገልሎቱ እየጨመረ ሲሄድ የኢትዮጵያ ቤተክርሰቲያን ተጀመረ የሚለው ስሜት እየሰፋ ሲመጣ የምዕመናኑ ቁጥር መበርከት መጀመሩ በክፍሉ ውስጥም የሚከናወነው የምግብ ሽታና የጽዳት ሁኔታ ግሪኮቹን ሰላሳሰባቸው ሌላ ቦታ እንደንፈልግ ተነግሮን ሌላ ቦታ ፍለጋ ተጀመረ።

በዚች ቤተክርስትያን ውስጥ በቀደምትነት ከነበሩት ሰዎች መካከል አቶ መንግስቱ፤ አቶ ኤርምያስ ፤ ወ/ሮ መሰረት ዳባ ፤ሻምበል ዘውዴ ፤ አቶ ግርማ ብሩ ፤ አማማ ፈቴ ፡ እማማ ሳራ ፤ እማማ ገነት ፤ አቶ ሰመረ ፡ አቶ ገብሬል የነበሩ ሲሆን እኔ በዛን ጊዜ በገንዘብ ያዥነት አገልግያለሁ በዛን ወቅት የነበረን ጠቅላላ ገንዘብ S300.00 ሲሆን ለካህናቱ አልፎ እልፎ ሃያ ወይም ሰላሳ ብር ይሰጣቸው እንደነበር ትዝ ይለኛል።

በዚህ ሁኔታ ውስጥ እያለን በኢትዮጵያ ያለው የፖለቲካ ሁኔታ ተቀይሮ ኤርትራ እራሷን የቻለች ሀገር ስትሆን በምዕመናን መካከል የሀሳብ ልዩነት መፈጠር ተጀመረ ወቅቱም የፀሎት ቤቱ ወደ ዲንኪ ታውን የሚዛወርበት በመሆኑ የኤርትራና የትግራይ ተወላጅ የሆኑ ምዕመናን ለመሄድ ፈቃደኛ ባለመሆን አባ ይስሃቅን ይዘው የራሳቸውን የፀሎት ቤት ለመከፈት ቢሞክሩም መነኩሴው አባ ይስሃቅ በቋንቋና በዘር እንደማያምኑ ኦርቶዶክሳዊ እምነታቸው የከርስቶስ ልጆች ሁሉ አንድ መሆናቸውን የሚያስተምር መሆኑን በማስረዳት ፈቃደኝነታቸውን ሳያሳዩ ቀሩ ። በዲንኪ ታውን በአባ ፍቀረማሪያም ካህንነት የተጀመረው ቤተክርስቲያን የዛሬው የደብረ ሰላም ቤተክርስቲያን ጥንሥስ ነው ማለት ይቻላል።

የሚኒሶታው የመጀመርያው ኢትዮጵያዊው ካህን አባ ይስሃቅ የተወሰኑ ጊዚያት በዲንኪ ታውን የተገኙ ቢሆንም ከሁለቱም ቤተከርስቲያኖች ተገልለው እሰከ ቅርብ ጊዜ እዚሁ ከተማ እንደነበሩ ወ/ሮ እንዬ አጫውተውናል።

# የሕንጻ ግንባታ አስተባባሪ ኮሚቴ ሪፖርት፡

የሕንጻ ኮሚቴ የግንባታውን ህልም እውን ለማድረግ ያለማቋረጥ በትጋት በመሥራት ላይ ሲገኝ በየወሩ በሁለተኛው ቅዳሜ በሚያደረገው ወርሃዊ ስብሰባ ብዙ ፕሮጀክቶቸን በመፍጠርና በመከታተል ጤናማ እንቅስቃሴ ለማከናወን ችሏል። በመስቀል በዓል አከባበር በርካታ ምዕመናንን አነቃቅቶ በማሳተፍ የተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀም ገንዘብ ለማሰባሰብ የተፈጠረው እንቅስቃሴና የተገኘው አመርቂ ውጤት ኮሚቴው ከምዕመናን ጋር እጅና ጓንት በመሆን እየሠራ ለመሆኑ በምሳሌነት መጥቀስ ይቻላል። በኮሚቴው ስር የተዋቀሩት አራቱ ንዑሳን ኮሚቴዎች የተለያዩ ፕሮጀክቶችን በመቅረጽ እና በመተግበር ላይ ሲገኙ እስካሁን ያከናወኑት ተግባራት በሚቀጥለው መልኩ ተቀናብሮ ቀርቧዋል።

## ፩-የህዝብ ግንኙነት ንዑስ ኮሚቴ፡

ሁ- የመጀመሪያውን የማዕዶት እትም አዘጋጅቶ ለምዕመናንና በቤተክርስቲያናችን ድህረ ገጽ ላይ አሰራጭቷል። ለህትመት ከወጣው ገንዘብ 80% በመስቀል በዓል ዝግጅት ወቅት ከፍቃደኛ አባላት በተገኘ ልገሳ የተሸፈነ ሲሆን ሁለተኛው ዕትም በተያዘለት የጊዜ ሰሌዳ መሰረት ተዘጋጅቶ ቀርቧል።
ለ- የሕንጻ ኮሚቴውን እንቅስቃሴዎች እና መረጃዎችን በማሰባሰብና በማጠናቀር ለምዕመናን በማቅረብ ላይ ይገኛል።
ሐ -በመስቀል በዓልና በምስጋና ቀናት የሕንጻ ኮሚቴውን እንቅስቃሴዎች በፖስተር በማዘጋጀት አቅርቧል
መ- የሕንጻ ግንባታውን እንቅስቃሴ በከተማችን በሚገኘው የኢትዮጵያ ሬድዮ እንዲሰራጭ አመቻችቷል
መ- የአስተያየት መስጫ ሳጥን አዘጋጅቶ አስተያየቶችን በመቀበል ግንባታውን ለማገዝ እየሠራ ይገኛል

## 2-የገንዘብ ማስገኛ ንዑስ ኮሚቴ፡

ሀ- ኮሚቴው አንድ ቡድን፤ አንድ አላማ፤ አንድ ግብ በሚል መርሆ በተጠናከረ መልኩ እየተንቀሳቀስ ያለ ሲሆን። በስሩም

- የዝግጅት አስተባባሪ
- የውጪ በጎ አድራጊዎች አስተባባሪ
- የበጎ ፍቃድ አገልግሎት አስተባባሪ
- የጥናት፣ ግምገማ እና ሪፖርት ዝግጅት አስተባባሪ ቡድኖችን አዋቅሯል

ለ- በ 2017 ዓ/ም በተለያዩ ዝግጅቶች በጠቅላላው $73,138.00 ፤ በዋሽንግተን ዲሲ ከሚገኙ አንድ ኢትዮጵያዊ በጎ አድራጊ $500.00 ፤ በዩኤስ ባንክ የነጻ አገልግሎት በመስጠት $58,198.00፤ ከታርጌት ፊልድ ነጻ እገልግሎት በመስጠት $65263.00 የነጻ ግልጋሎት ደርሻቸውን በገንዘብ ከተወጡ አባላት $3460 .00 በድምሩ$200,559.00 አሰባስቧል። በነጻ አገልግሎት የተገኘው ጠቅላላ ገንዘብ ከአባለት መዋጮ ጋር ሲነጻጸር 83% ያደርገዋል።

ሐ- ፈቃደኛ የሆኑ አባላትን በማሰባሰብና ስልጠና እንዲወስዱ በማድረግ እንዲሁም የነጻ እገልግሎቱ ስራ ሳይተጓጎል እንዲከናወን በማስተባበር 38 በታርጌት ፌልድ እንዲሁም 12 በዩኤስ ባንክ ግልጋሎቶች መስጠት ተችሏል።


መ- ፈብሯሪ አሰር ቀን በተለያየ መልኩ በቤተክርስቲያን ግንባታው ለተሳተፉ ምስጋና ለማቅረብ ባዘጋጀው የእራት ፕሮግራም ለግንባታው የሚውል ጨረታ በማከናወን ገቢ ማስገኘት ተችሏል

ሠ- የመስቀል በዓል ሲከበር አባላቱን በማስተባበር፣ ከምግብ (ቁርጥ፤ጥብስ፤ ሳንድዊች፡ በቆሎ፡፤እንጀራ ና ወጥ አና ሌሎች) ከመጠጥ (የታሸገ ዉሃ፤ ለስላሳ፤ ጠጅ፤ ሻይ ና ቡና) ፤ ጣፋጭ ና ስናክ በመሸጥ እንዲሁም የተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀም ገንዘብ ማሰባሰብ ተችሏል።

ረ- ለቤተርስቲያኑ ግንባታ በአባላት ውሳኔ በየአንዳንዱ እባላት ላይ የተጣለውን $5000 ብር መዋጮ ከፍለው ላጠናቀቁ እባላት የምሰከር ወረቅት እንዲሰጥ ተደርጓል።

ሰ- ከቤተክርስቲያኑ አባላት ውጪ ይህን የቤተክርስቲያን ግንባታ ሊደግፉ የሚችሉ በጎ አድራጊዎችን በማፈላለግ የቤተክርስቲያኑ የጀርባ አጥንት የሆኑትን አባላትን በማነቃቃት የተለያዩ ፕሮግራሞችን በመቅረጽ ላይ ይገኛል።

ሸ- ለቤተክርስቲያኑ ግንባታ በአባላት ውሳኔ በየአንዳንዱ አባል ላይ የተጣለውን $5000 ብር መዋጮ ከፍለው ላጠናቀቁ አባላት የምሰክር ወረቀት እንዲሰጥ ተደርጓል።



## 3. የ ፋይናንስ ንዑስ ኮሚቴ

ግልጽነት የተሞላበት ፤ ሳይንሳዊ የሆነ የገንዘብ አሰባሰብ አያያዝና አጠቃቀም ዘዴን በመጠቀም ፤በትክክለኛ መረጃ አደረጃጀትና መዝገብ አያያዝ ላይ ትኩረት በማድረግ የአባላትን መዋጮና የእለተ ሰንበት ሽያጭን በመከታተልና በማስተባበር የውስጥም ቁጥጥር በማድረግ እንዲሁም የግዥና የንብረት አያያዝን በመምራት እቅድ እና መርሃ ግብርም በማውጣት እየሰራ ይገኛል። ስራውንም ለማቀላጠፍ የተለያዩ የገንዘብ መሰብሰብያ እና መመዝገቢያ ቅጾችን ለኮምፒተር አጠቃቀም በሚመች መልኩ በመቅረጽ ጥቅም ላይ አውሏል።የሰንበት ቀን ሽያጭን በማስተባበር ቋሚ የገንዘብ ምንጭ ከመፍጠሩ ባሻገር ምዕመናን ያልተቋረጠ የገንዘብ ማሰባሰብ ሂደት እየተደረገ መሆኑን እንዲያስተውሉ በማድረግ ላይ ይገኛል። በፋይናንስ ኮሚቴው አሰተባባሪነትና በሌሎችም ኮሚቴዎች ተባባሪነት በምዕመናን ሰፊ ተሳትፎ የተገኘው የገንዘብ መጠን እና ምንጮቹ በሚቀጥለው ሰሌዳ ላይ ተጠናቅሮ ቀርቧል።

| | የገቢ ምንጭ | የተሰበሰበ መጠን |
|---|---|---|
| 1 | የአባላት መዋጮ | $205,025.00 |
| 2 | የበጎ ፍቃድ አገልግሎት | $126,921.00 |
| 3 | ከአባላት ስጦታ | $34,803.00 |
| 4 | ከአባላት ውጪ የተሰበሰበ ስጦታ | $21,767.00 |
| 5 | የሰንበት ቀን ሽያጭ | $44,132.00 |
| 6 | ከተለያዩ የገንዘብ ማስገኛ ዝግጅቶች | $73,138.00 |
| 7 | የምግብ ሽያጭ | $14,104.00 |
| 8 | ከሳንቲም ሳጥኖች | $4,361.00 |
| 10 | ጠቅላላ | $524,250.00 |

## 4. የንድፍ እና የግንባታ ንዑስ ኮሚቴ

ለግንባታው መጀመር አስፈላጊ የሆነውን የንድፍ ስራ ለማሰራት የጨረታ ሰነድ ባዘጋጀው መሰረት ሰማቸው ከዚህ በታች የተዘረዘረው አምስት ድርጅቶች

1-Lindborg Architecture and Design, PLLC

2-Sperides Reiners Architects, Inc. (SRa)

3-Rafferty Rafferty Tollefson Lindeke Architects (RRTL)

4-Armstrong Torseth Skold & Rydeen Inc. (ATS&R)

5-Close Associates Inc. Architects

ያቀረቡትን የጨረታ ሰነድ (proposal) በቅድሚያ ባዘጋጀው መስፈርት መሰረት ግምገማ በማካሄድ የቃለ መጠይቅናና የሥራ ቦታ ጉብኝት በማድረግ RRTL እና ATS&R የሚባሉትን ድርጅቶች ለሁለተኛው ዙር ውድደር እሳለፎ ATS&R የሚባለው ድርጀት

- ለቤተክርስትያኑ ጥያቄዎች በቂ መልስ በመስጠቱ እና ፍቃደኛ ሆኖ በመገኘቱ
- ባለው የቤተክርስቲያን ንድፍ የመስራት ልምድ
- ሥራዎችን በሰዓቱ በማጠናቀቅና በማስረከብ ሰላለው ልምድ በቂ መረጃ በማቅረቡ
- ለ መርሃግብርና እቅድ የጠየቁት ክፍያ አነስተኛ ሆኖ በመገኘቱ
- የጠየቀው የ7.6% የጠቅላላው ግንባታ ወጪ ክፍያ ከሌላኛው ድርጅት አንሶ በመገኘቱ
- በግንባታ ጊዜ በሚደረገው ግምገማ (inspection) በቂ ክትትል እንደሚያደርግ ማረጋገጫ በመስጠቱ ከከተማው አስተዳደር ፣ ከ Better Business Bureau (BBB) እንዲሁም በሙያው ዕውቅና ካላቸው ግለሰቦችና ድርጅቶች የድጋፍ ምስክርነት ለማቅረብ በመቻሉ

ሲመረጥ በቤተክርስቲያናችንና በድርጀቱ መካከል የቤተክርስቲያናችንን መብቶች በሚጠበቅ፤ የስራ ተቋራጩን ሀላፊነት በሚያብራራ መልኩ በባለሙያዎች የተዘጋጀው የውል ሰነድ ታህሳስ 15ቀን 2010ዓ/ም በቤተክርስቲያናችን አውደ ምህረት ላይ ስምምነት ተፈርሟል።

በዚሁ መሰረት የመጀመርያው ንድፍ በሚቀጥሉት ስድስት ወራት ተዘጋጅቶ እንደሚቀርብ ይጠበቃል። ይህም ለግንባታው ሂደት የመጀመሪያው ትልቅ እርምጃ ነው።





# በደስታ ያለፈ የምስጋና ቀን

አንዳንድ ቀናት የራሳቸው የሆነ የተለዩ የደስታና የምስጋና ቀናት ሆነው ያልፋሉ። ደስታ በተለያየ መልኩ ሊገለጽ የሚችል ሲሆን ብዙ ሰዎች በአንድ ወቅት ከውስጥ ከመነጨ ስሜት ተደምመው በአንድ አላማ በአንድ ግብ በአንድነት ሲነሳሱ ማየት ስሜትን የሚያባባ የፍቅርን ሀያልነት የሚቀርጽ እድመታ ትቶ ያልፋል።

ባለፈው ፌቡራሪ 10 ቀን በቤተክርስቲያናችን የሕንጻ ግንባታ ኮሚቴ አባላት በግል አነሳሽነት ከቤተክርሰትያኒቱም ሆነ ከሕንጻ ግንባታ ኮሚቲው ምንም አይነት ወጪ ሳይደረግ የኮሚቴውና የንዑስ ኮሜቴዎች አባላት ገንዘባቸውንና ጉልበታቸውን አስተባብረው ያዘጋጁት የእራት ግብዣና የተለያዩ ዝግጅቶችን ያቀፈው ፕሮግራም ከመቼውም ጊዜ በተለየ መልኩ በደስታ ያለፈ የምስጋና ቀን ነበር ቢባል ማጋነን አይሆንም።

በእለቱ እናቶች በአበሻ ቀሚስ ተውበው አባቶችና ጎልማሳ ወጣቶች የክት ልብሳቸውን ለብሰው፤ የቤተክርስቲያኑ ካህናት ካባቸውን ደርበው ፤ቀረ የማይባል የምግብ አይነት ተደርድሮ ፤ አዳራሹ ግጥም ብሎ፤ አስተናጋጅ የሚል የስም መለያ የለጠፉ የኮሚቴው አባላት ምእመናኑን ምን ይምጣ በማለት በትህትና ሲያስተናግዱ ማየት የምስጋና ቀኑን ከሌሎች ቀናት በበለጠ የመንፈስ አንድነት የታየበት ግሩም ቀን አድርጎት ነበር።

የምስጋናው ቀን የተጀመረው በቤተክርሰትያኑ አለቃ በመልከፂዮን ቀሲስ ሀዲስ ሞላ የምስጋና ፀሎት ሲሆን የእራቱ ፕሮግራም ከመጀመሩ ቀደም ብሎ የቤተክርስቲያኑ መዘምራን የተሰብሳቢውን ስሜት የሚያነቃቁ መንፈሳዊ መዝሙሮች አሰምተዋል። በመቀጠል የቦርዱ ሊቀመንበር አቶ መላኩ ወልደፃዲቅ የእንኳን ደህና መጣችሁ ንግግር በማደረግ በበጎ አድራጎት ፕሮግራም የተሳተፉትን ሁሉ አመስግነዋል። የዕለቱ ፕሮግራም አጋፋሪ አቶ አንዷዓለም እምሩ ታዳሚውን ፈገግ በሚያደርግና የዕለቱን መንፈስ በጠበቀ ዘይቤ ያደረጋቸው ንግግሮች እንዲሁም ያቀረባቸው ቀልዶች ባቀራረባቸውም ሆነ በይዘታቸው ፕሮግራሙን አሳምሮታል።

ቄሲስ ሀዲስ የምስጋና ቀንን ምክንያት በማድረግ የበጎ ፈቃደኝነትን አስፈላጊነት፤ ለቤተክርስቲያን የሚሰጥን የጉልበትና የገንዘብ ስጦታ በሚመለከት ካስረዱ በኋላ ቤተክርስቲያኗን የሚደግፉትን ሁሉ አመስግነዋል። ዶ/ር አሻግሬም የግንባታ ኮሚቴውን ስራዎችና የወደፊት ፕሮግራሞች ላይ ገለጻ አድርገዋል።

በዕለቱ የተገኙ ምእመናን ዶክተር አሻግሬ ላደረጉት ከፍተኛ አሰተዋጾ ያላቸውን አድናቆት ባገኙት አጋጣሚ ሁሉ በጭብጨባ ሲገልጹ የነበረ ሲሆን አንድ ምእመን ባንገታቸው አጥልቀውት የነበረን መስቀል በማውለቅ ሸልመዋቸዋል ። በዕለቱ በታርጌት ፊልድና በዩኤስ ባንክ ስታድዮም የላቀ ቀናት ለሰሩ ግለሰቦች ፤የገንዘብ ማሰባሰቡን ጥረት ለተባበሩ ድርጅቶችና ግለሰቦች እንዲሁም ቃል የተገባውን $5000.00 ከፍለው ለጨረሱ አባላት የምስክር ወረቀት ተበርክቷል። በዕለቱ ለጨረታ ቀርቦ በነበረው የተክሊል ካባ ላይ የተደረገው ውድድር የብዙ ሰዎችን ቀልብ የሳበ ሲሆን በጨረታው ከ37 ሺ ዶለር በላይ ገቢ ማሰባሰብ ተችሏል። በጥቅሉ ቀኑ መልካም ስሜት ጎልቶ የታየበት ቅንነት ቤተሰባዊነት የሰፈነበት ሆኖ አልፏል። የማዕዶት ዘገጀት ከፍል ተሳታፊዎች ይህን የተዋጣ ፕሮግራም ላዘጋጁ እህቶችና ወንድሞች የተሰማንን ምስጋናና ከበሬታ ለመግለፅ እንወዳለን።

በህብረት ዝማሬ በጋራ ፀሎት
እንደ አባቶቻችን ታሪክ ለመስራት
ተባብረን ባንድነት ሆነን በህብረት
በሰለሞን እድል በዳዊት ምኞት
በቅዱስ ቃሉ በፅሎት በወንጌል
ምሶሶ ይዘናል ጉልላት ልንሰቅል













የሕንፃ ግንባታ ኮሚቲ ዋና ፅሃፊ በመሆን ከፍተኛ አስተዋጽዖ ያደረጉት አቶ ዮሀንስ ዘውዴ በሥራ ምክንያት ወደ ሌላ ከተማ በመዛወራቸው የሕንፃ አስተባባሪው ኮሚቲ መልካም እድል እንዲገጥማቸው በመመኘት የመሸኛ ዝግጅት ሲያደርግላቸው በኮሚቲው የተዘጋጅም ሰጦታ በዐውደ ምህረቱ ላይ ተበርክቶላቸዋል። ማዕዶትም መልካም እድል እንዲገጥማቸው ትመኛለች።

